# <u>ህዳር - ቀይ እና ነጭ</u>

(በስመኝ ታደሰ)

Simegn Tadesse <simuadada8@gmail.com>

- *የአውሮፓ ህብረት፣ በ28ቱ የህብረቱ ሃገራት ያደረገው ጥናት እንደሚያሳየው በሀገራቱ ከሚኖሩ ከአምስት ሴቶች አንዷ የታዊ ወይም አካላዊ ጥቃት የደረሰባት ናት፤*
- *በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ዕድሜያቸው ከ12-16 ዓመት ካሉ ታዳጊ ሴቶች መካከል 83 በመቶ የሚሆኑት በት/ቤቶች ውስጥ ወሲባዊ ትንኮሳ ይፈጸምባቸዋል፤*

ወርሃ ህዳርን በርእሴ ከጠቀስኳቸው ቀለማት ጋር ያያያዝኩት ሁለቱም ቀለማት በሪባን ስለሚገለፁና የሁነቶች መታሰቢያ በመሆን አለም አቀፋዊ እውቅና ስላላቸው ነው። ቀይና ነጭ ሪባኖች ውክልናቸው ተቀራራቢ (ለሰብአዊ ጉዳዮች የቆሙ) ነገር ግን የተለያዩ መልዕክቶችን የያዙ ናቸው፡፡ እንደዛ፣ በአገራችን ተከስቶ እንደነበረው ክፉ ቀን፣ ቀይ ሽብር እና ነጭ ሽብር ፍልሚያ በተቃራኒ ጐራ ተሰልፈው እርስ በርስ መጠፋፋትን የሚወክሉ የእኩይ ተግባራት ተምሳሌቶች አይደሉም፡፡ "ቀይ/ነጭ ሽብር" ብል በታሪክ መዝገብ የዚህ ሰሞን አሰቃቂ አሻራ ትዝ አለኝ፡፡ በዚሁ ባለንበት ህዳር ወር 1967 ኢ.ም /ዛሬ 40 ዓመቱ/ ነበር ስልሳዎቹ የአፄ ኃይሌ ስላሴ ባለሥልጣናት በወታደራዊው የደርግ መንግስት ያለምንም ርህራሄ የተረሸኑት፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ኃብተወልድን ጨምሮ 60 ጐምቱዎች፣ አዛውንቶች እና ጥቂት ወጣቶች ታሪክ በማይረሳው ሁኔታ የጅምላ ግድያ ተፈፀመባቸው፤ ወታደራዊው መንግስት እስከ አገዛዙ ፍፃሜ ለብዙ ምሁራንና ወጣቶች ማጥፊያ ላደረገው የቀይ ሽብር አዋጅ መንደርደሪያና የደም እጁ ማሟሻ ያደረገውም እነዚህኑ ወገኖች ነበር፡፡ በወቅቱ የደርጉ ተቃዋሚና የተራማጅ ወጣቶች ስብስብ ነበር የሚባለው *ኢህአፓ* በበኩሉ በደርጐችና ሌሎች ባላንጣዎቼ ባላቸው ላይ *የነጭ ሽብር* የግድያ አዋጅን አውጆ የዜጎችን ደም ሲያፈስና ሲያፋስስ እንደነበር ታሪክ ያስታውሰናል፡፡

እዚህ ላይ ስለ ቀይ ሽብር እና ነጭ ሽብር (የታሪክ ጠባሳ ጥለው ያለፉ አሳፋሪ ክስተቶች) ያነሳሁት የተነሳሁበትን አጀንዳ ዘንግቼ ሳይሆን የሁለቱ ቀለማት ታሪክ/አገልግሎት እንዲሁም ማህበረ-ፖለቲካዊ ፋይዳ በህዳር ወር ካለው የታሪክ ትውስታ ጋር ስለገጠመበኝ ነው፡፡

ወደ ዋናው ርእሰ-ጉዳዬ ልመለስ፣ ይህ የህዳር ወር ሁለተኛ አጋማሽ ነጭ ሪባን በወንዶች እንዲሁም በመላው ማህበረሰብ ጾታዊ ጥቃትን ስለመከላከል/ማስቆም የሚታወስበትን እለት በማስመለከተ የሚደረግበ ሲሆን፣ የወሩ 22ኛ ቀን በበኩሉ ሁላችንም ቀዩን ሪባን በማድረግ የHIV/AIDS ቫይረስ ስርጭትን ስለመከላከል የምንወያይበት እለት መሆኑ ነው፡፡

የቀይ ሪባን ቀን ወይም የዓለም የHIV/AIDS ቀን በየዓመቱ ህዳር 22 መከበሩ ቫይረሱ ዓለማችን ላይ ያለውን ስርጭትና በአምራቹ የህብረተሰብ ክፍል ላይ እያደረሰ ያለውን ከፍተኛ ጥፋት፣ የልማት ኪሳራ . . . ባጠቃላይ አገራዊ ውድመት ለመቆጣጠር በማሰብ ሲከበር የቆየ “ቀን” ነው፡፡ (ቫይረሱ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ በሀገራችን ያደረሰው ጥፋት እጅግ ሰፊ የነበረ መሆኑንም እዚህ ላይ ማስታወሱ ተገቢ ይሆናል።)

ከጥቂት ዓመታት በፊት በሃገራችን በየመንደሩ የረገፈው ወጣት ብዛት፣ ያለወላጅ የቀሩ ህፃናትና በጨቅላነታቸው በሞት የተቀጠፉ ህፃናት ብዛት በቀላሉ የሚዘነጋ አይደለም፡፡ በተለያዩ ጊዜያት እንደ “ዝምታው ይሰበር”፣ “አንድም ሰው በHIV/AIDS እንዳይያዝ” እና የመሳሰሉ ዘመቻዎች ስለቫይረሱ በግልፅ መወያየት እንዲቻል በማድረጋቸው ዛሬ ላይ፣ በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ፈጥኖ ወደ ሞት የመሄድ፣ ከሰዎች የመገለልና፣ የመሳቀቅ ሁኔታዎች በከፍተኛ ደረጃ ቀንሰው ይስተዋላሉ፡፡

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በሚሊኒየሙ የልማት ግቦች የቫይረሱን የስርጭት መጠን ለመግታት ሊሰራበት በታቀደው መሰረት በርካታ ተግባራትን ካከናወኑ ሀገራት መካከል አንዷ በሆነችው በኢትዮጵያ ስርጭቱ እየቀነሰ ይገኛል፡፡

የፌዴራሉ የHIV/AIDS መከላከያና መቆጣጠርያ ጽ/ቤት ባሳለፍነው ዓመት መጋቢት ወር ላይ ያወጣው መረጃ እንደሚጠቁመው በሀገሪቱ ዕድሜያቸው ከ15-24 ዓመት ከሆኑ ወጣቶች መሀል በቫይረሱ የሚጠቁት መጠን በየወቅቱ እየቀነሰ በመሄድ ላይ ይገኛል፡፡ በጥናቱ ላይ እንደተመለከተው የስርጭት መጠኑ:-

በ1999 3.3 በመቶ

በ2001 2.6 በመቶ

በ2004 ወደ 2.3 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡

ሌላውና በዚህ ፅሁፌ ልገልፀው የፈለኩት አቢይ ጉዳይ የነጭ ሪባን ጉዳይ ነው። በአለም አቀፍ ደረጃ፣ ነጭ ሪባን የወንዶች የቃል ኪዳን ምልክት ነው፡፡ ቃል ኪዳኑም በሴቶች ላይ ፆታዊ ጥቃቶችን ላለመፈፀም፣ ሲፈፀምም ዝም ላለማለትና ለመከላከል የሚያኖሩት መሐላ ነው፡፡ በየዓመቱ በህዳር ወር 2ኛ አጋማሽ ማለትም ከህዳር 16 እስከ ታህሳስ 1 ቀን ባሉት ቀናት ይከበራል፡፡ በነዚህ ቀናት ወንዶች በሴቶች ላይ ፆታዊ እና ወሲባዊ ጥቃት እንደማይፈፅሙ መሃላቸውና ቃልኪዳናቸው ያረፈበትን ነጭ ሪባን በማንገት ቃላቸውን ያድሳሉ፡፡

ነጩ ሪባን፣ ፆታዊ ጥቃት በአንድ ማህበረሰብ ባጠቃላይም በአንድ ሃገር ሁለንተናዊ ገፅታ ላይ የሚያሳርፈውን ጫና ለመቀነስ ብሎም ለማስቆም ታልሞ የተፀነሰ ሃሳብ ነው፡፡ ፆታዊ ጥቃት በአብዘኛው ወንዶች በሴቶች እና በህፃናት ላይ የሚያደርሱት ስነ-ልቦናዊ እና አካላዊ ጫናና በደል ሲሆን፣ ቁጥሩ ያን ያህል ባይሆንም ድርጊቱ በሴቶችም እንደሚፈፀም የመስኩ ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡ በመሆኑም የነጭ ሪባንም ሆነ እለቱ፣ በአብዛኛው የጥቃቱ ሰለባ የሆኑት ሴቶች ላይ ያተኩር እንጂ በማንኛውም ወገን ማለትም የስርአተ-ፆታ አባላት ላይ የሚፈፀምን ማንኛውንም አይነት ጥቃት/በደል በፅኑ ያወግዛል፤ ይቆም ዘንድም ይታገላል።

ወደ አገራችን እንመለስ፤ በሃገራችን በነበሩ ነባር ልማዶች ምክንያት የስርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት (Gender justice) እጦት፣ የአንድ ስርአተ-ፆታ አባላት የበላይነት . . . ወዘተ ሲንፀባረቅ የኖረ ሲሆን በዚህ ሳቢያም በርካታ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ተከስተዋል፤ በተለይም ጠለፋ፣ ግርዛትና የጉልበት ብዝበዛን በመሳሰሉ ፆታዊ ጥቃቶች የሴት ስርአተ-ፆታ አባላት እጅግ ሲሰቃዩ፣ ተፈጥሮአዊና ሰብአዊ መብቶቻቸው ሲጣሱ ኖረዋል፡፡ ይህ ዛሬም አልቆመም፤ አለ።

ጾታዊ ጥቃት መልኩ ቢለያይም በሁሉም የዓለም ሀገራት በሚኖሩ ሴቶችና ህፃናት ላይ የሚፈፀም ድርጊት ነው፡፡ በያዝነው የፈረንጆች ዓመት የአውሮፓ ህብረት የሰብዓዊ መብቶች ኤጀንሲ (Europen Union Agency for Fundamental Rights) በ28 የህብረቱ ሃገራት ላይ ጥናት ጥናት በማድረግ ባወጣው መረጃ እንዳመለከተው ከአምስት ሴቶች አንዱ ፆታዊ ወይም አካላዊ ጥቃት ይደርስባታል፡፡ በሌላ በኩል፣ በመላው ዓለም በተለያዩ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ምክንያቶች በእናቶች፣ ሴቶች፣ ልጃገረዶችና ህፃናት ላይ የሚደርሱ

ጥቃቶች፣ የሚፈጠሩ ጫናዎች እና የመብት መነፈጎች  የተለያየ መጠን ይኑራቸው እንጂ ችግሩ የሁሉም እና በሁሉም ዘንድ ያለ መሆኑን በርካታ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተለይም ጦርነትና የሰላም መታጣት ለችግሩ መባባስ ሁኔታዎችን ሲያመቻች ይስተዋላል፡፡ የናይጄሪያው አማፂ ኃይል የቅርብ ጊዜ ሁኔታ ለዚህ ማሳያ ሊሆነን የሚችል አስከፊ ክስተት ነው፡፡ የአማፂ ቡድኑ ያነገበው አጀንዳ፣ ምንም አንኳ ፖለቲካዊ ቢሆን እጅግ በርከት ያሉ ታዳጊ ህፃናትን/ተማሪዎችን እና ሴቶችን አፍኖ በመውሰድ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ፈፅሞባቸዋል፡፡ ለተጨማሪ ግንዛቤ ይረዳን ዘንድ፣ የሰላም መጓደል በአንፃራዊነት ለፆታዊ ጥቃት መባባስ መንስኤ ለመሆኑ በግልፅ ከሚያስረዱ ሁኔታዎች መካከል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ያወጣቸውን መረጃዎች እንመልከት፤

- ከአስር ዓመታት በፊት በሩዋንዳ ተከስቶ በነበረው የርስ በርስ ግጭት ምክንያት በሶስት ወራት ብቻ የአንድ ሚሊዮን ያህል ሰዎች ህይወት የተቀጠፈ ሲሆን በወቅቱም ከ250 እስከ 500  ሺህ የሆኑሴቶች የአስገድዶ መድፈር ድርጊት ተፈጽሞባቸዋል፡፡
- ከ1992-1995 በቦስኒያና ሄርዞጎቪኒያ መካከል በተካሄደው ጦርነት 50 ሺህ የሚጠጉ ሴቶች ፆታዊ ጥቃት ተፈፅሞባቸዋል፡፡
- እንደ አውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ከ1991-2001 በሴራሊዮን የኮር አንጃዎች መሃል ተፈጥሮ በነበረው ግጭት ወቅት ከተፈናቀሉና በመጠለያ ከነበሩ ስደተኞች 50 ሺህ የሚሆኑ ሴቶች ተገደው ተደፍረዋል፡፡
- በዲሞክራቲክ ሪፖብሊክ ኮንጎ ባለው የርስ በርስ ብጥብጥ፣ እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር ከ1996 ወዲህ ቁጥራው ከ200 ሺህ የሚልቁ ሴቶች በዚሁ አደጋ ተጋላጭነት ተመዝግበዋል፡፡

ከነዚህ መረጃዎች መረዳት የሚቻለው ስርአተ-ፆታን መሰረት ያደረገ፣ በሴቶች ላይ እየደረሰ ያለ ጥቃት የከፋና አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን ነው፤ ጦርነትና የርስ በርስ ግጭት መኖር ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በባሰ መልኩ ሴቶችና ህፃናትን ለከፋ ስቃይና እንግልት የሚዳርግ መሆኑንም ጭምር።

ከላይ የተመለከተውን መረጃ ከጦርነትና ሰላም እጦት ጋር አያይዘን የፆታዊ ጥቃትን አስከፊ ገፅታ አነሳን እንጂ ሰላማዊ በሚባሉ ሀገራት (አካባቢዎች)ም ቢሆን በሴቶች ላይ የሚደርሰው የሰብአዊ መብት ጥሰት በቀላሉ የሚታይ አይደለም፤ ምናልባት ፆታዊ ጥቃቶች ባለመማር ወይም ደግሞ በስልጣኔ ወደኋላ መቅረት ምክንያት ብቻ የሚከሰት

ድርጊት አድርገን የምንወስድ ሰዎች አንታጣም፤ ነገር ግን እውነታው እህ አይደለም። ችግሩ ይህ ብቻ አለመሆኑን የሚያሳዩ መረጃዎች በርካታ ሲሆኑ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሪፖርት አንዱ ነው።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በዚሁ ጾታዊ ጥቃትን አስመልክቶ ባደረገው ጥናት ከፊተኛቸው የዓለም ሃገራት መካከል አሜሪካና ኬኒያ የሚጠቀሱ ሲሆን የሪፖርቱ ጭመቃሳብም የሚከተላውን ይመስላል:-

- በናይሮቢ 20 በመቶ ሴቶች በስራ ገበታቸው ላይ ያታቸውን ብቻ መሰረት ያደረገ ወሲባዊ ትንኮሳ ይደረግባቸዋል፡፡ ይህ ቁጥር እንደ ጃፓን፣ ፊሊፒንስ፣ ማሌዥያ እና ደቡብ ኮሪያ ባሉ የኤዢያ ሃገራት ከ30 - 50 በመቶ ይደርሳል፡፡
- በዩናይትድስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ዕድሜያቸው ከ12 - 16 ዓመት ካሉ ታዳጊ ሴቶች መካከል 83 በመቶ የሚሆኑት በት/ቤቶች ውስጥ ወሲባዊ ትንኮሳ ይፈጸምባቸዋል፡፡

ችግሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚባባስና ሰለጠኑ በተባሉ ሃገራትም እየባሰበት በመሄድ ላይ መሆኑ የሚያስተምረን ነገር ቢኖር እኛ ኢትዮጵያውያን አጅግ ትልቅ የቤት ስራ እንዳለብን/የሚጠብቀን መሆኑንና ከተኛንበትም እንነቃ ዘንድ የሚቀሰቅስ ደወል (alarm) ነው፡፡

ከነዚህ ቁጥሮችም በላይ አንዳንድ ስነምግባር የጎደላቸው የማህበረሰብ አባላት በሴቶች ላይ እያደረሱት ያሉት ዘግናኝ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት፣ አላስፈላጊ ጫና . . . ዛሬ ዛሬ እየተበራከተ መምጣቱን ባይናችን በብረቱ እየተመለከትን እንገኛለን፡፡ በሀገራችን አሲድ የተደፋባቸው፣ በአደባባይ የጥይት ዶፍ የዘነበባቸው፣ በፍቅረኞቻቸው አሰቃቂ ግድያና አካል ማጉደል የተፈፀምባቸው ወዘተ ወዘተ ሴቶችን በሚዲያ መስማት አሁን አሁን እየተደጋገመ ብቻ ይሆን እየተለመደ የመጣ የዘመናችን ሰቅጣጭ እውነታ ሆኗል፡፡ ሁኔታው እየከፋ. . . እየከፋ . . . እየከፋ ሄዶ ይህው ዛሬ የደረሰበት (የደረስንበት) ደረጃ ላይ ደርሷል ለዚህ ማረጋገጫችን ደግሞ የታዳጊ ህፃን (gang rape victim የሆነችው) ሃና ላላንጎ ህልፈተ ህይወት ነው።

ሰሞኑን በመዲናችን አዲስ አባባ ከደረሱት አደጋዎች (የትራፊክም ይሁን ሌላ) ሁሉ እጅግ አሳዛኙ፣ አሰቃቂ፣ ህዝብን ከዳር እዳር ያሳዘነ፣ ከነባር ኢትዮጵያዊ ባህል የፈነገጠ፣ ማህበራዊ እሴትን የሚሸረሽር . . . ተግባር ቢኖር በሴት እህቶቻችንና ልጆቻችን ላይ

እየደረሰ ያለው ከግልም ያለፈ ቡድናዊ ፆታዊ ጥቃት ሲሆን እሱም በቡድን የመድፈር /gang rape/ እና የመግደል አፀያፊና አረመኔያዊ ተግባር ሆኖ እናገኘዋለን። ይህ በሚያስደነግጥ፣ ለማመን በሚያስቸግር መልኩ የተፈፀመ የግፍና ጭካኔ ድርጊት የ10ኛ ክፍል ተማሪዋንና የ16 ዓመቷን ታዳጊ ለህልፈተ ህይወት አብቅቶ ከቤተሰንብ እስከ የሰው ልጆች ሁሉ ድረስ አሳዝኗል፡፡ምንም አልነው ምንም፣ ማንም አዘነ ማንም ድርጊቱ ተፈፅሟል፤ ታዳጊ ሃናም ላትመለስ ሄዳለች።

ግን አንድ ጥያቄ አለ። በተለይ እኛ የሴት ስርአተ ፆታ አባላት የወንድ ስርአተ ፆታ አባለትን ልንጠቃቸው የምንፈልገው አንድ ጥያቄ አለ:-

*ላለፉት 8 እና ከዚያ በላይ ለሁኑ ዓመታት ሴትን ልጅ ከማጥቃት ለመታቀብ/ላለመፈፀም ብቻ ሳይሆን በሴት ልጅ ላይ የሚደርስን ማንኛውንም አይነት ጥቃት ጭራሹኑም ለማስቆም ቃል በመግባት ነጩን ሪባን ሲያንጠለጥሉ የኖሩት የሃገራችን ወንዶች ቃላቸው ምነው ተሰበረ፤የትስ ወደቀ? የሚል።*

በአርግጥ ሪባኑም ሆነ ትርጉሙን ያለመረዳታችን የፈጠረው ችግር ሊሆን ይችላል፡፡ ዓለም ለ23 ዓመታት፣ ኢትዮጵያም ለ9 ዓመታት እለቱን ስናከብር፣ ድርጊቱን ስንኮንና የድርጊቱ ሰለባዎችን ስንዘክር ቆይተናል፤ ችግሩ ምንም አይነት መሻሻል አለመታየቱ ላይ ነው። በአንድ ዓመት ውስጥ ካሉ 52 ሳምንታት ሁለቱን ብቻ ቀንሰን ስለፆታዊ ጥቃት የምንነጋገር ከሆነ፣ አንዲት ሴት ወይም ህፃን አሰቃቂ ጥቃት ሲደርስባት ጠብቀን ብቻ "ሆ?" የምንል ከሆነ ችግሩ አልተሰማንም ማለት ነው፡፡ ልብ ብለን ካስተዋልን ባለፉት ጥቂት ዓመታት ጐላ ብለው ከሰማናቸው፣ በቤተሰቦቻቸውና በወንዶች አሰቃቂ ጥቃት የተፈፀመባቸው ሴቶች ድርጊቱ የተፈፀመው እዚሁ እመዲናችን አዲስ አበባ ውስጥ ነው - የአፍሪካ መዲና የምንላት አዲስ አበባ ውስጥ፡፡ አሁንም ደግመን እንጠይቃለን፤ *ለመሆኑ ነጩ ሪባን መልዕክቱን አስተላልፏል ወይ?*

እንደኔ አስተያየት ማህበረሰባችን በራሱ ባህልና ዕሴት ለሴት ልጅ ለሚያደርገው እንክብካቤ ተገቢውን ዕውቅና ብንሰጥ (ችግሩን ባይፈታውም) የድርጊቱን መጠን ከዚህ መቀነስ የምንችል ይመስለኛል፡፡ የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻና ግርዛትን የመሳሰሉ ነባር ጐጂ ልማዶችን በትምህርት ተቀብሎ እየቀነሰ ያለው ማህበረሰብ /አልተማረም ተብሎ የሚታመነው/፤ ሴቶች ያለፍላጐታቸው ጫፋቸው የማይነካባቸው ባህሎችም እንዳሉት ማወቅና ማሳወቅ አለብን፡፡ ለምሳሌ በመንገድ፣ በገበያም ሆነ ወንዝ የወረደች ሴትን ያለፍቃዷ ጨርቋን የነካን ወንድ በሃገር ሽማግሌዎች የሚያወግዙ ብሎም መቀጫ

የሚጥሉበት ስርዓት ያለ መሆኑን በመጥቀስ፣ በምሳሌነት ተወስደው ቢስፋፉ ቀሪው ማህበረሰብ የሴትን ልጅ ክብር እንዲረዳና እንዲያምን ለማድረግ ቀላል መንገድ ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡ በየመንግስታዊ መዋቅሩ፣ በየትምህርት ተቋማቱ . . . ያሉ የስርዓተ-ፆታ ቢሮዎችና ጽ/ቤቶችም ካሉበት የሰመመን ጉዞ ነቅተው ተግባራቸውን መወጣት አለባቸው እላለሁ፡፡

**ሪባኖች ሆይ ወዴት አረፋችሁ**???????